# የአውሮጳ ሸንጎ

## የአውሮጳ ሸንጎ አባላት

ብራስልስ፤ ታህሳስ ፳ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም፤

እኛ ስማችን ከዚህ በታች የተጠቀሰው ይህንን ደብዳቤ የምንጽፍልዎት የግል ጋዜጠኛና ጸሐፊ የሆነውን እስክንድር ነጋ ያላቋረጠ እስር በተመለከተ የተሰማንን ለመግለጽና ባስቸኳይ መፈታት እንዲችል እርስዎ መንገዱን እንዲያመቻቹ በጥብቅ ልናሳስብዎ ነው፡፡

ለረጅም ጊዜ አሳታሚና ጋዜጠኛ የሆነው አቶ እስክንድር በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪቃ ይፋ እየሆነ ስለመጣው የአረብ ጸደይ እንቅስቃሴ በግልጽ በመጻፉ በአገሪቱ በ፪ሺ፩ዓም በወጣው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ተከስሶ በ፪ሺ፬ ዓም ታስሯል፡፡ አቶ እስክንድር ምንም እንኳን የእንቅስቀሴው ደጋፊ ቢሆንም ተመሳሳይ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ መካሄድ እንዳለበት ያለማቋረጥ አጽንዖት ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ግን ከእርስዎ በፊት የነበረው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መንግሥት አቶ እስክንድርን በቁጥጥር ሥር አውሎ ለአንድ ወር ያህል ከቤተሰቡ ጋር ሳይገናኝ፤ ለሁለት ወራት ያህልም ከጠበቃ ጋር እንዳይገናኝ በማድረግ በመጨረሻ የአስራስምንት ዓመት እስራት ፈርዶበታል፡፡ በአሁኑ ጊዜም ባለቤቱና ህጻን ልጁ እየኖሩበት ያለውን የአቶ እስክንድርን ቤት ለመውረስ ሁኔታዎች እየተመቻቹ መሆኑንም ዘገባዎች ይጠቁማሉ፡፡

አለመታደል ሆኖ አቶ እስክንድር ብቻ ሳይሆን ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ በአሸባሪነት ክስ ተመስርቶባቸው የረጅም ዓመታት እስር ተበይኖባቸዋል፡፡ የእርስዎ መንግሥት በ፪ሺ፩ዓም ያወጣውን የጸረ አሸባሪነት አዋጅ በጋዜጠኞችና የተቃዋሚ መሪዎች ላይ እያዋለው መሆኑን የአፍሪካ የሰውና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር እንዲሁም ጸረ አሸባሪነትንና ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ ልዩ ራፖርተር የሆነውን ጨምሮ አምስቱ የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ራፖርተሮች በዚህ ዓይነቱ አሳሳቢ አካሄድ ላይ የማስጠንቀቂያ ሃሳባቸውን ገልጸዋል፡፡ አንዳንዶቹም ግልጽ ያልሆነ የጸረ አሸባሪ አዋጅ በተግባር በማዋል በተገቢ ሁኔታ ራስን ለመግለጽ የሚደረገውን አካሄድ ዝም ለማሰኘት መጠቀም በቀጣናው ያለውን እርግጠኛ የደኅንነት ስጋት ተዓማኒነት በጽኑ እንደሚያራክሰው ጠቁመው ነበር፡፡

የአቶ እስክንድርን ጉዳይ በተመለከተ በቀጣይ የሚካሄዱ የይግባኝ ሁኔታዎች እንዳሉ ስለምንረዳ የሕጉ ሂደት እንዲቀጥል የእርስዎን አስፈላጊነት የምናከብረው ነው፡፡ ሆኖም ግን ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት የሕዝባዊና የፖለቲካ መብቶች ዓለምአቀፋዊ ቃልኪዳን አንቀጽ ፲፱ ላይ በተካተተው በተለምዶ በዓለምአቀፋዊ ሕጎች ላይ የተጠቀሰውን ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት መብት የማክበር ኃላፊነት የእርስዎ መንግሥት ግዴታ ነው፡፡

www.goolgule.com

ስለሆነም እርስዎ አሁን ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብቶች ወደፊት እንድትገፋና ከመንግሥታት ማኅበረሰብ ውስጥ በሙላት እንድትንቀሳቀስ የመምራት ልዩ ዕድል አጋጥሞታል፡፡ በመሆኑም በሥልጣንዎ ያለውን ሁሉ በመጠቀም አቶ እስክንድር በአፋጣኝና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈታ ዘንድ እንዲያመቻቹ በጥብቅ እናሳስብዎታለን፡፡

በእውነት የእርስዎ

ከማይነበብ ፊርማ ጋር የደብዳቤው ፈራሚዎች፡-

እስክንድር ግራፍ ላምብስዶርፍ

አና ጎሜዝ

ቻርልስ ታኖክ

ኤዱዋርድ ኩካን

ኤጃ-ሪታ ኮርሆላ

ኤሚሊዮ ሜኔንዴዝ ዴል ቫል

ፍራንክ ኢንግል

ኪንጋ ጋል

ላዒማ ሉሲያ አንድሪኬን

ማሪያ ዳ ጋርሳ ካርቫልሆ

ማሪያ ጋብሪኤል

ማይክል ጋህለር

ኖርበርት ኑሰር

ያል ሽሚት

ዴቪድ ማርቲን

**ትርጉም፡- ጎልጉል፡ የድረገጽ ጋዜጣ፤ ታህሳስ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.**
Translator: Golgul: the Ethiopian Internet Newspaper
www.goolgule.com
editor@goolgule.com

ጎልጉል: የድረገጽ ጋዜጣ www.goolgule.com